# ዕውን “መድረክ” ይሰነብት ይሆን?

ዘአማን በላይ

bzaman@yahoo.com

“መድረክ” የተሰኘው ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፖርቲዎች የመሰረቱት የፖለቲካ ግንባር ከትናንት ዛሬ፣ ከዛሬ ደግሞ ነገ ይሻለዋል ሲባል እንደ ካሮት ቁልቁል እያደገ መሆኑን ሰሞነኛው የአመራሮቹ ውዝግብ ይፋ አድርጎታል፡፡ ስብስቡ እየተፍረከረከ መሆኑንም ጭምር። ምንም እንኳን የአመራሮቹ ፖርቲዎች ጥምረትን የናፈቁትና በጋራ ለመሥራት ከአራት ዓመታት በፊት በጥድፊያ መክረው በጋራ ለመንቀሣቀስ የፈቀዱት የሚያግባባቸው የጋራ ጉዳይ ወይም አጀንዳ ኖሯቸው ሣይሆን፤ ገዥውን ፖርቲ በሌለ ማንነት ለመገዳደር ከተቻለም ለመጣል የሚያስችል አጋጣሚ ከተገኘ ቢል ስልጣን ናፋቂነት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡ እናም ይህ የግንባሩ ቀዳሚና ሰሞነኛ ክስተት ዕውን መድረክ የሰነብት ይሆን? የሚል ጥያቄን እንዳነሳ አድርጎኛል።

እርግጥ “ከአንድ ብረቱ ሁለት መድኃኒቱ” እንዲሉ ከተናጠል ይልቅ የወል አሠራር ጥሩ እንደሆነ ሣይታለም የተፈታና በተግባር የተመሰከረለት በመሆኑ ግንባር መስርተው መንቀሣቀሳቸው ክፋት የለውም፡፡ ክፋቱ ያለው “የትም ፍጪው ስልጣኑን አምጪው” እንዲሉ ዋነኛውና ኢ-ጤነኛ ህልማቸው የሆነውን ስልጣንን በማለም በአቋራጭ ዙፋን ላይ ለመውጣት ሲሉ እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዓይነት ፀረ-ኢትዮጵያ ተቋማት ሳይቀር ለባዕዳን በማደርና አንጋሽ ፍለጋ ለማግኘት በገዛ ሀገራቸው ላይ በባንዳነት ተግባር መሰለፋቸው ነው። ዓላማቸው ይህን የቀን ቅዠታቸውን ማሳካት በመሆኑ ግንባር ለመመስረት የጥድፊያ ወዳጆች ሆነዋል። ዳሩ ግን እነዚህ ጉደኞች ለመግባባት ምኞት እንኳን ያልፈጠረባቸው ብቻ ሳይሆኑ ሣት ብሏቸው እንኳን ስምምነትን የማይመርጡ እንዲሁም በሰማይም ሆነ በምድር መግባባት የማይችሉ የስድስት ዓለም ፓርቲዎች ስብስብ ናቸው፡፡

እንደ “ሽሮ ፈሰስ” መድረክን በጥቂት ጊዜያት ውስጥ አፍልተው ለግንባርነት ያበቁት የድርጅቱ አመራሮች እርግጥም እንኳንስ ኢህአዴግን ያህል በሳልና ባለ ራዕይ ድርጅትን ቀርቶ፣ በውሃ ቀጠነ ጠዋት ማታ የሚጨቃጨቁ ጥንድ ጐረቤቶችን እንኳን

ለማለያየት የሚያስችል የአጣይነት "ጥበብ" ያልቀሰሙ፤ ይልቁንም በጠንካራ ተቀናቃኝነታቸው ምትክ ራሣቸውን ማሰንበት የሚያስችል አመራር እንደ ሰማይ ርቋቸው እርስ በእርሣቸው በአካልና በቃላት ሲቧቀሱ እየተመለከትን ነው–ፈርዶብን፡፡

"የምንትሴ ባል ከምንትሴ አያስጥልም" እንዲል የሀገራችን ሰው፤ ምግባራቸው ሁሉ 'እንዳይሆን፣ እንዳይሆን' ዓይነት ሆነና አሳስተዋቸውም ይሁን ወይም ተሳስተው ከጐናቸው የቆሙ ጥቂት ደጋፊዎቻቸውንም አንገት እያስደፉ ነው፡፡ እርግጥ እነዚህ እፍኝ የማይሞሉ ደጋፊዎቻቸው የግንባሩን አዝማሚያ ቃል በቃል እየተገነዘቡ በመጡ ቁጥር በጣት የሚቆጠሩት ደጋፊዎቻቸው "አይናችሁን ላፈር" በማለት ግንባሩን ባዶ እንዳስቀሩት ማንም የሚረዳው ሃቅ ነው፡፡ መድረክ እንኳንስ ከህዝቡ ጋር የሚጣጣሙ ቀርቶ ከጥላቸው ጋርም የሚጣለዙ አመራሮች ግንባር መሆኑን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይረዳዋል፡፡ የግንባሩ አመራሮችም ይህን ሃቅ እየመረራቸውም ቢሆን ተቀብለውታል– ከመሰንበቻውም እየመሰከሩ ነው።

ወትሮም ቢሆን ለመግባባት ምለው ተገዝተው በይድረስ ይድረስ ጭብጨባ ጥምረትን የፈጠሩት የመድረክ ቁንጮዎች ሰሞኑን ደግሞ አዲስ የማወዛገቢያ አጀንዳ አግኝተዋል፡፡ እናም እንደ ድሮው በቦክስ ባይሆንም በቃላት መወራረፋቸውን ተያይዘውታል፡፡ ለነገሩ ቀደም ሲልም "የጣቴ ጠላት ወዳጄ ነው" በሚል የተበላበት እቁብ ለይምሰል አንድነትን አጥልቀው ኢህአዴግን በአሉባልታ ለመፋለም በፖለቲካ ንግድ ተዋዋሉ እንጂ፤ በባህም ሆነ በምግባር የሚቀራረቡ እንዳልሆኑ ምግባራቸው ይመሰክራል፡፡ ጠዋት ማታ በነገር ወንጭፍ እየተወራወሩ መሳቂያና መሳለቂያ ያደረጋቸው ይኸው የውዴታ ግዴታ ጋብቻቸው ነው፡፡

አንድ እንዲያደርጋቸው ድንገት የጠፈጠፉት መድረክ ከግንባርነቱ ይልቅ ልዩነቶቻቸውን አግዝፎት የጥምረቱን አመራሮች ማስመዘንና ማስገመት ይዟል– አለመግባባታቸውን፡፡ አንዱ የድርጅቱ አመራር እንቁም ሲል ሌላኛው እንተኛ፣ ቀሪው እንትከል ሲል ከፊሉ እናጥፋ የሚሉ ዓይነት ግራና ቀኝ የማይግባቡ ግለሰቦች የተሰገሰጉበት ተቋም ነው፡፡ ልብ እንበል! የግንባሩ ውስጣዊ እንከኖችና አለመደማመጥ፣ ከፍ ሲልም ከአብሮነትና ከአንድነት ይልቅ ለመበታተንና ለመጠፋፋት ቅርበት ያላቸው ብሎም ከቶም ለአቅመ ጥምረት ያልበቁ የፖለቲካ ፖርቲዎች ስብስብ መሆኑን ለመመስከር የግድ የፖለቲካ ተንታኝ መሆንን አይጠይቅም፡፡ እርስ በእርሣቸው የሚበላሉትን የግንባሩን አባል ድርጅቶች መግለጫዎች፣ እሮሮዎች፣ አሉባልታዎች እንዲሁም የትምና መቼም

የማይታረቁ ፕሮግራሞቻቸውን /ምናልባትም ካላቸው ማለቴ ነው/ መፈተሽ ብቻ በቂ ይመስለኛል፡፡

እስቲ ለአብነት ያህል የመድረክ አንድ ክንፍ ወይም አባል ድርጅት የሆነው አንድነት ፓርቲ ሰሞኑን ለአንድ ወር አጥንቼዋለሁ ያለውን "ጥናት" እንደ አንድ ታማኝ እማኝ እንጥቀስ– እስከ ዛሬ አድምጠን የግንባሩን ህፍረተ- ምግባሮች ያጤንንባቸውን አለ-ባልታዎችን ሳንዘነጋ፡፡ አንድነት ፓርቲ በጥናቱ የመድረክ ህገ-ደንብ ዴሞክራሲያዊነት ያልፈጠረበት መሆኑን በማስታወስ የእናት ድርጅቱን ገመና ዘክዝኳል፡፡ ፓርቲው አውቆም ይሁን አዳልጦት እርግጠኛ መሆን ባይቻልም፤ መድረክ ለተቃናቃኝነት የሚያበቃውን ዴሞክራሲያዊ እሣሳቤ የህገ-ደንቡ ማዕቀፍ አለማድረጉን በመጥቀስ በተዘዋዋሪ የራሱንም ባዶነት ጠቁሟል፡፡

የአንድነት "ጥናት" በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ ግንባሩ ዴሞክራሲያዊነት እንደራበው ደግሞ ደጋግሞ ያተተው አንድነት ድርጅቱ በየትየለሌ ችግሮች የተተበተበ መሆኑን መስክሯል፡፡ የመድረክ መሪዎች ብቃት እንደሚጐላቸውም አልደበቀም፡፡ መድረክ ወደ ግንባርነት ያደገው በዘፈቀደ መሆኑንና የግንባር አወቃቀር መርህን የጣሰ ነው ሲልም ራሱን ያለበትን ድርጅት ተችቷል፡፡ አንድነት ፓርቲ ሃቁን በአደባባይ መመስከሩ ለእውነት መቆሙን የሚያመለክት ባለመሆኑ ባያሸልመውም ግና አያስወቅሰውም፡፡ አንድም አንድነት ራሱ የመድረክ አካል ነውና "ጂላጦሳዊነትን" የማታ ማታ ቢያማትር ንፅህናውን ወይም የተሟሟተ መስመር አለመከተሉን አይጠቁምም፡፡ እናም ይኸው ፓርቲ ከተራ አለ-ባልተኝነተና ቅንጣት ያህል ለሃገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ግብዓት በመሆን ፈንታ፤ በበሬ ወለደ የመንደር ፖለቲካ ባባከነው ጊዜው ታሪክ እንደሚጠይቀው እገምታለሁ፡፡

የመድረክን ገመና ለማጋለጥ የተነሣው አንድነት ብቻ አይደለም፡፡ መድረክ አየደለም ሀገርን ያህል ታላቅና ረቂቅ አካል ማስተዳደር ይቅርና በአይንህ ቀለም አላማረኝም ዓይነት ፀብ የለሽ በዳቦ ነገር እያፈላለጉ እርስ በእርሳቸው የሚቧቀሱና የሚደባደቡ የስድስት ዓለም ክስተቶች ስብስብ መሆኑን አባል ድርጅቶቹ ሁሉ በየፊናቸው ተቀምጠው በአንድ በኩል ግንባሩን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተዘዋዋሪ ራሣቸውን እየረገሙ ነው፡፡ የግንባሩ አካል ናቸውና የግንባሩ ውድቀት የአባላቶቹም ጭምር ነውና፡፡

ከአባል ድርጅቶቹ የሚሰነዘሩት “ፀረ-መድረክ” ትችቶችና አሉባልታዎች፣ ስድቦችና ክሶች ላስተዋለ የግንባሩ አመራሮች፤ እንኳንስ በሀገራዊ ጉዳይ አብረው ለመስራት የመከሩ ፖለቲከኞች ይቅርና አንድ ቀን እንኳን ለሻይ ቡና ተገናኝተው የሆድ የሆዳቸውን የተጨዋወቱ ወዳጆች እንኳን አይመስሉም፡፡ ብስለት የለም፡፡ አስተዋይነት የለም፡፡ ግብረ-ገብነት የለም፡፡ ምግባራቸው ሁሉ ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች በነሲብ እንደምትመታ ኳስ አበደች ነገር ይመስለኛል– ሁሉም የተሰማውን በመወርወር በነገር መጣለዙን ቀጥሏል፤ ፖለቲካ አበደች፡፡ እንገመታለን–እንመዘናለን–እንቀላለን ብሎ ነገር የለም፡፡

በእኔ እምነት አንድነት የግንባሩን ግልብነት መገምገሙ፤ ገምግሞም ለማጋለጥ መሞከሩ መልካም ነገር ነው፡፡ ይሁንና ዳር ዳር ማለቱ ከግንባሩ ለመሰናበት ሰውነቱን እያሟሟቀ ለመሆኑ ያመለክታል፡፡ ለምን ቢሉ መድረክ ለአቅመ ግንባርነት የማይበቃ ወይም በአንድነት አነጋገር የግንባሩ ቁመና “ራስ ሣይጠና ጉተና” በመሆኑ በጊዜ ለመሰናበት ማቀዱ አይቀርም፡፡  ዳሩ ግን አንድነት የግንባሩን ሃፍረተ- ምግባር ለማጋለጥ ቢሞክርም ዶክተር መረራ ጉዲና ግን ስለ ግንባሩ ታላቅነት ለመሞገት ፈልገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዶክተሩም ቢሆኑ የፓርቲውን /የአንድነትን/ ጥናት ቢያጣጥሉም ቅሉ "የመንገድ ላይ ሥራ" በሚትል ቀሽም ማስተባባያ የግንባሩን ውድቀት ለመደበቅ አልቻሉም፡፡

የግንባሩ አባል ድርጅቶች ማለትም የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ /ኦህኮ/ እና የኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፌዴን/ ሊቀመንበር ዶክተር መራራ ለመድረክ በመሞገት የአንድነትን ትክክለኛ ግምገማ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ለማጣጣል ቢሞክሩም፤ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ ግንባሩ ለአራት አመታት ምግባር አልባ እንደነበርና ችግሮችም እንዳሉበት አልካዱም፡፡ መድረክን በጋራ መጠለያነት የመረጡት አባል ፖርቲዎች በባህሪም ሆነ በምግባር ለየቅል ናቸውና አንድ ሆነው ሣለ እርስ በእርሣቸው ቢላተሙም የሚገርም አይደለም። መድረክ ጊዜያዊ ምሽጋቸው፤ ኢህአዴግን ለማስወገድ ይረዳቸው እንደሆነ በማሰብ አቋቋሙት እንጂ በስጋም ሆነ በደም የማይዛመዱ ዓይነት ባዕዳን ናቸውና በአንድነታቸው ውስጥ አንድነት ቢታጣበት እርግጥም አይደንቅም፡፡

ያም ቢሆን ግን ሃቁን እንዳለ ለመደፍጠጥ መሞከር ተገቢ አይደለም። ትዝብት ላይም ይጥላል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ መድረክን እንደሚያውቀው፤ መድረክ ዶክተሩ የሰቀሉትን ያህል የተጨበጨበለት ሣይሆን የተጨበጨበበት ድርጅት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ

ተመዝኖ ብዙ ጊዜ ቀሏል፤ ወድቋል፡፡ በነውረኛና ራዕይ አልባ አመራሩ በኩል የግንባሩን ቁም ነገር አልበኝነት ዜጎች ተገንዝበዋል፡፡ ተገንዝበናል፡፡ ከሁሉም የሚገርመው የዶክተሩ መስተባበያ የግንባሩ ችግሮች የሚመነጩት ከሀገሪቱ ፖለቲካ መሆኑን መጥቀሳቸው፤ በሌላ አባባል በኢህአዴግ ለማሳበብ ዳር ዳር ማለታቸው ነው፡፡

ዶክተሩ ለውድቀታቸው ምክንያት የሀገሪቱ ፖለቲካ መሆኑን መውቀሳቸው በራሱ የሚያስወቅሳቸው ነው። ለምን ቢሉ ግንባሩ የሀገሪቱን የፖለቲካ ምህዳር ለመውቀስ ጣቱን በሌላ ላይ ከመቀሰሩ በፊት ራሱ የሚጠበቅበትን ሣይሆን ከሚጠቅበትም እንኳን በታች አልሞከረምና፡፡ ይልቁንም የሀገሪቱን ፖለቲካ ከማሳደግ ይልቅ ለማኮስስ ተግቶ የሠራና እየሠራ ያለ ራዕይ አልባ የፖለቲካ ጥምረት በመሆኑ ራሱን ከተጠያቂነት ለማሸሽ ሌሎችን ለማብጠልጠል ያለምንም ማቅማማት መጠቋቆሙ ስህተት ነው፡፡ ይህን ለማድረግ የሞራልም ይሁን የሥነ- ምግባር ድፍረት የለውም፡፡ ምናልባትም "የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ" እያለ ሊሆን ይችላል፡፡

ዶክተሩ የሀገሪቱ ፖለቲካ እያሉ የሚያብጠለጥሉት የትኛውን ረቂቅ አካል እንደሆነ ባይገባኝም፤ ገዥውን ፓርቲ ለመውቀስ ዳር ዳር ማለታቸው እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ የሀገራችን ፖለቲካና ፖለቲከኞች መድረክና የመድረክ አባል ድርጅቶችንም ጭምር ያካትታል– ምንም እንኳን በጥላቻ ፖለቲካ ተጀቡነው መንቀሳቀስ ባለመቻላቸው ለአቅም ፖለቲካኝነት ባይበቁም፡፡ በአንድ በኩል መድረክ በችግሮች የተተበተበ መሆኑን አባል ድርጅቶቹ ራሳቸው ያለምንም ማቅማማት እየመሰከሩ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለችግር የዳረገን ገዥው ፓርቲ ነው ይላሉ፡፡ ለውስጥ መፍረክረካቸው ምክንያቱ ኢህአዴግ እንደሆነ አድርገው ጣታቸውን ለመቀሰር መሞከራቸው ኢ-ምክንያትያዊነት የገነዘው ቀሽም ማስተባበያ ይመስለኛል፡፡ በእኔ እምነት መድረኩ ሌሎችን በማይመለከታቸው ጉዳይ የግድ እየጐተተ ተጠያቂ ለማድረግ ከሚርበተበት ለውድቀቱ ምክንያቱ ራሱ መሆኑን እየመረረውም ቢሆን መጋት ያለበት ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም መድረክ የረባ የፖለቲካ መስመር እንኳን የሌለው መሆኑን የአንድነት ፓርቲን ጥናት በደምሳሳው ልጠቀምና የግንባርን አመሠራረት መርህ እንኳን የማያሟላ እንዲሁም ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት የሰፈነበት ድርጅት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነውና፡፡

እርግጥ ነው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታችን ለጋ በመሆኑ ፍፁም ከህፀፅ የፀዳና የሚያመፃድቅ ላይሆን ይችላል፡፡ በዓለማችን ቢሆን ፍፁም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

እንደሌለ ሊሰመርበት ግድ ይላል፡፡ ዴሞክራሲ ሂደት ነውና ጊዜንና ትውልድን ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ ጥቃቅን የአፈፃፀም ጉድለቶች ቢኖሩ የተጓዘናቸውን ተስፋ ሰጭና የመስመራችንን ትክክለኛነት የሚመሰክሩ ዕውነቶችን እንዳለ ለመደፍጠጥ መውጣትና መውረድ ግን አንድም በሳል ተሚጋች አያስብልም ወይም ያስፎርሻል፡፡ ችግሮች ካሉም የጋራችን እንጂ ተቢድንና የእናንተና የእኛ የምንላቸው አይደሉም፡፡

ምናልባት ዶክተሩ ሃቁን ለመሸፋፈንና የመድረክን ህልውና /ያችኑ ጭል ጭል የምትለውን/ ለማሰንበት አልመው ሊሆን ይችላል፡፡ ማንም የሚገነዘበውን ያገጠጠና ያፈጠጠ ችግር /ግመል ሰርቆ አጐንብሶ/ ለመደባበቅ የሚታገሉት ዶክተር መረራ የግንባሩን "ምግባረ- ሰናይነት" በቃል ቢያሰማምሩትም በተግባር እየሆነ ያለውን እኛ ዜጐች እናስተውላለንና ሊያምታቱን ከሆነ ሞኝነት ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ ዶክተሩ የተላተሙት ከራሣቸው የፖለቲካ ሽርክ /ከአንድነት/ ጋር ብቻ አይደለም፡፡ የመድረክ ግራ ክንፍ አባል ድርጅት የሆነው የአረና ፖርቲ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራትንም ተቃውመዋል። ምክንያቱም አቶ ገብሩ በተዘዋዋሪም ቢሆን መድረክ አጣብቂኝ ውስጥ መግባቱን በመጥቀስ የአንድነትን ጥናት የሚጋሩ መሆኑን በገዳምዳሜው መስክረዋልና፡፡ ሁሉም የግንባሩ አባል ድርጅቶች መድረክን የመገምገምና አሠራሩን እንዲያሻሽል ገንቢ አስተያየት የማቅረብና የመተቸት መብት እንዳላቸው በማውሳትም ጭምር፡፡

ዳሩ ግን አንድ ማንም የማይክደው ነጭና ጥቁር ሃቅ በግንባሩ መካከል ስለተደነቀረ አባል ድርጅቶቹ በሃሳብም መግባባት እንደማይችሉ ግልፅ ነው፡፡ እናም ሰሞነኛ መተረማመሳቸውና እንደ ሰፈር ልጆች አጥር ጥግ ተቀምጠው የነገር ድንጋይ መወራወራቸው አይገርምም፡፡ አንድ ግንባር ውስጥ ሰፍረው በቋንቋም ሆነ በንድፈ ሃሣብ ለየቅል መሆናቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ የመድረክ አባል ድርጅቶች በተግባርም በመርህም አንድ መሆን ሲገባቸው ድንበር ከልለው በነገርም በአካልም ለመቧቀስ የተነሱት በእርግጥም ወደው አይደለም –ተገደው እንጂ። ወትሮም ቢሆን ግንባር መፍጠርን የናፈቁት ከሚያግባባቸው ይልቅ የማያግባባቸው ጉዳይ የትየለሌ መሆኑ ጠፍቷቸው አይደለም፡፡ ይልቁንም "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" በሚለው የነተበ ቀመር በመመራት ካላቸው የሥልጣን ጥማትና ጠኔ በመነሣት ነው፡፡ "የፖለቲካ ቁር ከምንትሴ ሣያስታቅፍ አይቀርም" መሰል የስድስት ዓለም ፍጡራንን በአንድ 'የፖለቲካ' ጐጆ አሰባስቦ ያባላቸው ይዟል።

ጉዳዩን ዘርዘር አድርገን ብንፈትሸው መልካም ሳይሆን አይቀርም። ነገርን ማጤን ደግ ነውና፡፡ መድረክን በፖለቲካ ውህድነት መርጠው ለአብሮነት የታደሙበት አባል ድርጅቶቹ አንድም ሀገራዊ ራዕይ ያልነደፉና የአየር በአየር ፖለቲከኞች በመሆናቸው አሊያም የሰማይና የምድርን ያህል የተራራቁ ውትፍትፍ ኢ-ኢትዮጵያዊ አጀንዳዎችን ያነገቡ በመሆናቸው ይደማመጡ ካልሆነ በስተቀር ምግባራቸውም ሆነ ቃላቸው ቢዥጐረጐር አያስደንቅም፡፡ ወትሮም አንድ ባለመሆናቸው አንድነትን እንዲያምጡ ማስገደድ አይቻልምና፡፡

የግንባሩ አባል ድርጅቶች በእርግጥም እዚያና እዚህ ተንፈራጠው የቆሙ ለየቅል ክስተቶች ናቸው፡፡ አንዱ የብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን ልዕልና በመደፍጠጥ አሃዳዊነትን /ደርጋዊነትን/ የሚያቀነቅን ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ እንዲሉ ፌደራሊዝምን ያለ ቡድን መብት ጠፍጥፎ ለመጋገር የሚጣደፍ ነው፡፡ የቡድኖቹ ዥንጉርጉርነት በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፡፡ ከፊሉ የኒዮ-ሊዝኒሊዝም አገልጋይ መስሎ ለመሰለፍና ኢትዮጵያዊነትን ጉሊት አውጥቶ ለመቸርቸር ያሰፈሰፈ ሲሆን፣ ከፊሉ ደግሞ እንደ ሽሮ ፈሰስ በድንገት የደረሰ የፖለቲካ መስመር አራማጅ ነው፡፡ የግንባሩን ምግባረ ዝርክርክነት ለመገንዘብ የአሠራሩን የዘወትር የእርስ በእርስ በሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት የሚያደርጉትን መቧቀስ ማጤን ብቻ በቂ ነው፡፡ ኢህዴግን ከመንበረ ሥልጣኑ ለማስወገድ ብቻ ካላቸው ግልብ ፖለቲከኝነት በመነሣት የማይግባቡ ቢሆንም፤ ለመግባባት ባደረጉት ያልተጠና ሽርክና መሳቂያና ማሳለቂያ ለመሆን ተገደዋል፡፡

እውነቱን ለመናገር መድረክ የፖርቲዎቹን ውስጠ ነገር ወይም ሃፍረተ ምግባር ለመሸፋፈን የሚያስችል አሠራርም ሆነ ብስለት የለውም፡፡ የግንባሩን አመራሮች አባባል ቃል በቃል ልዋስና ግንባሩ ለአቅመ ግንባርነት እንኳን የበቃ አይደለም፡፡ ድርጅቶቹ መድረክን ያቋቋሙት እንደ ሰፈር እግር ኳስ ቡድን ድንገት እየተጠራሩ እንጂ ሰከን ያለ ምክክርና ኘሮግራም ቀርፀው ባለመሆኑ፤ ኢህአዴግን ለመጣል ብቻ በማሰብ የቀመሩት ደራሽ የፖለቲካ ተቋም ኢህአዴግን ይቅርና ከእንደኔ ዓይነቱ ተራ ዜጋ ትዝብት እንኳን አላዳናቸውም። የመድረክን መፈረካከስና ምግባረ ዥንጉርጉርነት ያጋለጠው የአመራሮቹ ፖለቲካዊ ብስለትና አቅመ ቢስነት እንዲሁም ራዕይ አልባነት ብቻ አይደለም፡፡ መድረክ የዴሞክራሲ ባህል ድርቅ የመታው የአመራሮች ቤት መሆኑን አንድነት በእርግጥም

አብጠርጥሮ በጥናቱ አስረድቷል፡፡ ምንም እንኳን የግንባሩ አመራሮች በአደባባይ የምናስተውለውን ሃቅ በማስተባበል የአንድነትን ጥናት ለማድበስበስ ቢሞክሩም፤ የመድረክ አባል ድርጅቶች መቻቻልና መደማመጥ ብሎ ነገር፣ ግብረ ገብነት፣ ሆደ ሰፊነትና ትዕግስት ያልፈጠረባቸው ግልፍተኞች መሆናቸውን ደግሞ ደጋግሞ መናገር ከሚዛናዊነት የሚያርቅና ትዝብት ላይ የሚጥል አይመስለኝም፡፡ እንዲያውም የአባል ድርጅቶቹን አመራሮች ምግባር ሳስተነትን ፍፃሜው አያምሬ "የትራጀዲ ፊልም" ተዋናዮች እንጂ ሃገር ለመምራት ሰውነታቸውን እያማሟቁ ያሉ ፖለቲከኛ መስለው አይታየኝም–ኧረ አያድርግብን!... ሰርከ ውዝግብ ነው፡፡ ጠዋት ማታ መናቆር ነው፡፡ በጥቅሉ መቻቻል የሚባል የዴሞክራሲ ባህል ፈፅሞ አልፈጠረባቸውም፡፡

ከዚህ ይልቅ የሚያወዛግባቸውና የሚያናቁራቸው ገዥው ፖርቲ እንደሆነ ዘወትር ለመለፈፍ ይሞክራሉ። አንዳንድ ጊዜ የመድረክ አመራሮችን ሳጤናቸው ኢህአዴግ አራት ኪሎን ያለ አንዳች ምርጫ እንዲያስረክባቸው የሚናፍቁ ይመስለኛል፡፡ ኢህአዴግ ፖርቲ ነው፡፡ ኢህአዴግ ምንም እንኳን ከመድረክ ጋር ዝቅ ብሎ የሚወዳደር ባይሆንም በፖለቲካ ፖርቲነቱ በመርህም ብቻ ሳይሆን በተግባርም ከመድረክ ልቆና ገዝፎ ለመገኘት መውጣትና መውረዱ የሚያስወቅሰው አይመስለኝም፡፡ ያን የማድረግ መብትም ሆነ ግዴታ አለበት፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ኢህአዴግ አጣላን ይሉትን ቀሽም ክስና መሠረት- ቢስ ውንጀላ እንድናዝንባቸው እንጂ እንድናዝንላቸው አያደርገንም፡፡

የመድረክ አባል ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው የማይስማሙ ሆነው ሳለ፤ ኢህአዴግን እንደ ምክንያት ማንሳታቸው ተገቢነት የለውም፡፡ ምናልባትም የሚያጣላቸው አካል ካለም መድረኮች ያለ መጣለት "ጥበብን" ተክነውና በልጠው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የመድረክ አመራሮች ወደ ፖለቲካው "ሪንግ" ዘለው በመግባት እርስ በእርሳቸው የሚናረቱ ከሆነ ግን በእኔ እምነት ብስለት ጉድሏቸዋልና ተጠያቂዎቹ ራሳቸው ናቸው፡፡ እናም ለማመን፤ ሃቁን ለመካድ የማንቸኩል ከሆነ መድረክን የሚጠብቀው ራሱ ኢህአዴግ ነው፡፡ ኢህአዴግ ባይኖር የመድረክ አባል ፖርቲዎች እንደ እፍኝነት እርስ በእርሣቸው ተበላልተው መተላለቃቸው አይቀርም ነበር፡፡ ጦሣቸውም ለእኛም መትረፉ አይቀርም ነበር፡፡ ለምን ቢሉ በእድሜም ሆነ በትምህርት ከኔ ቢጤ አላዋቂ ዜጋ አስር እጅ እንደሚያስከነዱ የሚነግሩን "ታላላቅ" ፖለቲከኞቻችን ለመደማመጥና ለመቻቻል የሞራልም፣ የህሊናም፣ የእምነትም፣ የሥነ-ምግባርም አቅም የላቸውም፡፡ መቼም ከምግባረ የቀደመ ሁነኛ ታማኝ

እማኝ የለምና ሆደ-ሰፊነትንና መቻቻልን ያልቻለ፣ የዴሞክራሲ ባህልን ያስተምራል ማለት ሰማይን የመቧጠጥ ያህል አስቸጋሪ ነው፡፡

እናም በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት የአረና ፖርቲ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራት እንዳሉት የግንባሩን ስር የሰደደ ውስጣዊ ችግር ለመቅረፍ፤ ቢያንስ ቀስ በቀስ ኢህአዴግን የሚገዳደር ድርጅት ሆኖ ለመቅረብ ውስጥን ማጥራት፣ ዜጎችን ማማለል የሚችል የፖለቲካ ፕሮግራም መንደፍና ከዜጎች የተሻለ በሣልና አርቆ አስተዋይ አመራር መፍራት ይኖርበታል፡፡ የሚበጀን፤ ለሀገርና ለትውልድ የሚፈይደው መቻቻላችንንና አንድነታችንን ይበልጥ የማያጠናክር፣ ብዙህነታችንን የሚያጐለብትና የተጀመሩ የሠላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ፕሮግራሞችን ይበልጥ አጠናክረው የሚያስቀጥሉ ተግባሮችን ነድፎ የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት መታገሉ ነው፡፡ ያኔ ህዝብ የትኛው ከየትኛው ፖርቲ ተመራጭ መሆኑን ይመሰክራል፡፡ አሁን ባለንበት ወቅት ግን ከኢህአዴግ የሚቀድም ባለ ራዕይ የፖለቲካ ፖርቲ ገና አልተፈጠረም፡፡

በመጨረሻም የመድረክ አመራርና የፓርላማ አባል የሆኑት አቶ ግርማ ሰይፉ ሰሞኑን በተናገሩት ትዝብት ምልከታዬን ላጠናቅቅ፡፡ የመድረክ አመራሮች ሀፍረተ-ምግባር ያሳፈራቸው የተከበሩ አቶ ግርማ "ኢህአዴግ እኛን ለማፈን ካለው ጥንካሬ ይልቅ እኛ ለመታፈን ያለን ዝግጁነት እየበለጠ መጥቷል" ብለዋል። እውነት ነው የመድረክ አመራሮች አንዱ አንዱን ረግጦ በሥልጣን ሽኩቻ የበላይ ለመሆን ተፍ ተፍ ከማለት ይልቅ፤ ህዝብ ተመራጭ እንዲያደርጋቸው ቢተጉ መልካም ይመስለኛል። እነርሱ ቢንቁትም ሿሚውም፤ ሻሪውም፤ አንጋሹም ሆነ አኩሳሹም ህዝብ ነውና፡፡ እናም የተከበሩ አቶ ግርማ ካሉት ዕውነታ በመነሳት ለድንጋይ ጠያቂው ውሃ እንደሚያቀብለው የማይግባቡ ግንበኞች ስብስብ ዓይነት የሆነው የመድረክ ቁርኝት እስከመቼ እንደሚሰነብት የሚወስነው በአመራሮቹ መካከል በሚኖረው የስልጣን ጭቅጭቅ ጡዘት ብቻ ነው። አበቃሁ።